# ፊትህ የትኛው ነው?

በአዲስ ተስፋ

ሞከርኩኝ ሞከርኩኝ ፊትህን ለማየት፣

ወስብስብ ሆነብኝ በቅጡ መለየት ።

ሰው የመሰለውን እውቅ ማንነትህን ፣

ካጣልኸው በኋላ ስታውልቅ ጭንብሉን ።

ጅብ ነው አሉኝና ላምናቸው ስሞክር ፣

ሰማሁኝ በጅቦች ለመፍረድ ስትፎክር ።

ሌቦችን መጠበቅ ወይም መከላከል ፣

ሰራየ አይደለም አልችልም ላስጠልል ።

ማንስ ነገራቸ ው ተልከስከሱ ብሎ፣

አናደርግም እኛም ለጅቦች ተጋድሎ ።

ስትል ሰማሁና ጅብነትን ስትንቅ፣

ባለሁበት አገር እኔም ሆኜ ከሩቅ ።

ስለዚህ ደስ ብሎኝ ማመስገን ስጀምር፣

ቃልህን አጠፍከው ሳትውልም ሳታድር ።

እኛን ሌቦች ያሉን በተንኮል ተጣምረው፣

ሃይል አልባ ሊያረጉን ሊያንበረክኩን ነው፣

በህዝብ ማንነት ላይ በጎሳችን ቀንተው ።

ሰላም ልማታችን መጥቆ ስለሄደ፣

ለፖለቲካ ትርፍ በእኛ ተነገደ ።

በማለት ቋንቋህን በአንዴ ለዎጥክና ፣

ቆመህም ተገኘህ ለጅቦች ጥብቅና ።

ማንነቴን ነኩት ጎሳየን ደፈሩ፣

በማትም ፎከርክ ደነፋህ በአገሩ።

ከጅብነት ወጥተህ ሌላ ገጽ አወጣህ፣

በመንደርህ ታጠርክ በዘውግህ ተሸፈንህ።

በሌላው ገጽታህ በነገድ ጉረኖ ፣

መሰለህ ምስጢሩ የሚቀር ተዳፍኖ ።

እናማ ህዝብህን መሸሻ አድርገህ፣

እንደ አምበሳ ደቦል መኩራራት አማረህ ።

አምበሳም ነው ብየ ፊትህን ፈለግሁት ፣

ነገር ግን መሰለኝ የትንሿን ድመት ።

ለምንስ እንዲህ አልህ ብለህ ብትሞግተኝ፣

ሆ ብሎ ሲዘምር ራያ ሲያገሳ፣

ዐማራ ነኝ ብሎ ወልቃይቴው ሲነሳ ።

ሲሸልል ብትሰማ ገና ድምጽ ሲያዎጣ፣

ዐማራ ማምረሩ መቁረጡ ሲገባህ፣

ወዴትም አቅጣጫ ማምለጫ እንደሌለህ ።

ብሶት ባበገነው ዙሪያህን ተከብበህ፣

ከንቱ ጩኸት ነበር ጦርነት ማለትህ፣

ዙሪያህን አስበህ ልብህን መዝነህ፣

የጦርነት አዋጅ የወራት ቅስቀሳህ፣

በቆፈሩት ጉድጓድ መቀበር ቢያሰጋህ፣

ሰላምን ሰባኪ እርግብ ሆነህ መጣህ ፣

ታዲያ እንዴት ልወቅህ የትኛው ነው ፊትህ ።

ከጅቦች ማህበር ወይስ ከአምበሶቹ?

ከቆርጣሚ አይጦች ወይ ከድመቶቹ?

ከብልጣብልጥ ጦጦች ወይስ ከተኩላዎች ?

ሰላምን ዝማሪ ከሆኑት እርግቦች ?

ዝምዳህ ከየት ነው ፊትህ የትኛው ነው?

ብዙ መልኮች ይዘህ ህዝቡንም ሸዎድከው ።

© በአዲስ ተስፋ

ጃንዋሪ 2019